ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በየካቲት 12 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## የጦር መሳሪያ ጋጋታ ሠላምን አያመጣም !

በአሁኑ ወቅት፤ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አስጊ ሁኔታ ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ማዕዘናት፤ ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ ዓይነቱና ብዛቱ የማይታወቅ የጦር መሳሪያ በገፍ እየገባ ነው ። ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ስለሚገባ ፤ በሀገሪቱ ላይ ለተለያዩ ችግሮች ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል ። ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሚደረገውም ጥድፊያ ፤ ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ፤ ለተለያዩ አሸባሪ ቡድኖች መጠቀሚያ እንዲሆን መፈቀዱ ነው ። ወያኔ ኢሕአዴግ የመሳሪያ ሽያጩ ዋናው መሆኑ ደግሞ ጥርጥር የለውም ። ሠላምና መረጋጋት አለመኖር ፤ በሕዝብ ሠላማዊ ሕይወት ላይ ይኸ ነው የማይባል አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ። ስጋትና ፍራቻ፤ ጥላቻና ዕርስ በርስ አለመተማመንን አስፍኗል። በሠላም ወጥቶ መግባት የሚናፈቅበትን ጊዜ ፈጥሯል ። አልፎ-ተርፎ፤ በዜጎች መካከል የአንድነት መንፈስ በይበልጥ እየተሸረሸረ መምጣቱን አመልካች ሆነዋል።

በውጭና በውስጥ፤ ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚጥሩ ኃይሎች በሀገራችን ላይ የቱን ያኽል የጥፋት ትብብር እንዳላቸው የሚጠቁም ብዙ ምልክቶች እየታዩ እንደሆኑ ግልጽ ሆኗል ። የጦር መሳሪያው በኮንትሮባንድ እየጎረፈ በመምጣቱ ምክንያት፤ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ያስከተለው ደንቃራ የቱን ያኽል ተፅዕኖ እንዳሚኖረው በትክክል መናገር የሚችሉት በሙያው የተካኑ ኢኮኖሚስቶች ብቻ ሳይሆኑ፤ ጉዳቱ በየአንዳንዱ ቤት ገብቶ የሚቸገረው ዜጋ ጭምር በጥልቀት አስግቶታል ።

የጦር መሳሪያ አምራች ሀገሮች ፤ ኢትዮጵያን የሸቀጣቸው መጣያ አድርገዋታል። በዚህም፤ የጦር መሳሪያ ነጋዴዎች፤ አዘዋዋሪዎችና ኮንትሮባዲስቶች ዋና ተጠቃሚዎች ሆነዋል ። ሁነኛ ተቆርቋሪ ባለቤት የሌለው ኅብረተሰብ፤ ሀብት ንብረቱ፤ የአልፎ- ሀጅዎች መጠቀሚያ መሆኑ የማይቀር በመሆኑ፤ ሀገራችንም የዚህ አጋጣሚ ሰለባ ሆናለች ቢባል ማጋነን አይደለም ።" **ባለቤቱን ሳይንቁ አጥሩን ማነቃነቅ"** እንደማይሞከር ሁሉ፤ ጠንካራ መንግሥት የሌለው ሀገርና ሕዝብም ፤ የመጣ የሄደው ሁሉ እንዳፈተተው ይቀልድበታል ። የሀገርን ሉዐላዊነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል ።

ሁነኛና ጠንካራ መንግሥት በሌለበት ሥር ዓተ -አጋዛዝ ስር የወደቀ ሀገርና ሕዝብ ፤ ነፍጥ የጨበጠ ማነኛው ቡድን ሁሉ ያላንዳች ስጋት ያሻውን የሚፈጽምበትን ሁኔታ ይፈጠርለታል። ዛሬ በሀገራችን የሚታየው ሀቅ ይኸ ነው። በብሔር ብሄረሰብ አደረጃጀት መድበል፤ ጦር መሳሪያ ይዞ በሀገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ኃይል ፤ የየክልል አገዛዝን አቋቁሞ፤ የየግሉን ነፍጠኛ- ጎጠኛ አገዛዝ መስርቷል ። ታጣቂ ኃይሎችን የሚቆጣጣጠሩ በየቃጠናዎቹ አሰማርቷል ። ይኸ ሁኔታ በማዕከል ደረጃ አገዛዝ ነኝ የሚለውን ተቋም፤ ጥርስ የሌለው ዱዳ እስኪያስመስለው ድረስ ሥልጣኑን አኮላሽቶታል። ዛሬ በሀገራችን የፖለቲካው መልከዐ- ምድር ፤ የኃይል ሚዛናቸው ተመጣጣይ ነው ባይባልም እንኳ፤ ቢያንስ ቢያንስ እርስ በእርሳቸው የሚፏከቱ ሦስት ተፃራሪ ኃይሎች ተከስተዋል። እነርሱም፡-

**1ኛው** የሕዝብ ትግል ጠልፎ፤ ለውጥ አመጣሁ የሚለው ጎራ ነው ። ይኸ ጎራ ሥልጣን የተቆጣጠረ ቢሆንም፤ የተለያዩ ችግሮችና ደንቃራዎችን በበቂ ችሎታ መቆጣጠር ተስኖታል ቢባል፤ የሚያሳየውን ጥረት ማጣጣል ነው ማለት አይደለም ። የማነኛውም መንግሥት ተቀዳሚ ተግባር፤ የሀገሩን ሠላምና የዜጎቹን ደኅንነት መጠበቅ እንደሆነ ቢታወቅም፤ አዲስ አበባ ያለው አገዛዝ ፤ግዴታውን በተሟላ መልኩ ሊወጣ አልቻለም ። የዚህ ምክንያትም ፤ በብሄርተኝነት ደረጃ ተደራጅተው ፤ መሳሪያ ታጥቀው በመንቀሳቀስ፤ የሠላማዊ ዜጎችን ሕይወት እያደፈረሱ፤ ንፁሃንን እየገደሉና እያፈናቀሉ ያሉ ፀረ አንድነት እንቅስቃሴዎች በመኖራቸው እንደሆነ ግልፅ ሆኗል ።

**2ኛው.** በጎጥ- በብሄር የተደራጀውና የታጠቀው ክፍል ፤ " **ሲፋጅ በሚንኪያ ፤ ሲበርድ በእጅ** " በሚል ይትበኃል ወስጥ የሚዋዥቀው ኃይል ነው። ቁርጠኛ የሆነ ሀገራዊ ተልዕኮ ሊኖረው እንደማይችል፤ በድርጊቱና በትረካው እያስመሰከረ እንደሚገኝ የአደባባይ ምሥጢር ከሆነ ቆይቷል ። ከተሳካለት ፤ ሀገራዊ አጀንዳ ያለውን ኃይል እያሰናከለና እያዳከመ የራሱን አጀንዳ የበላይነት ለማስፈን ባልተፈቀደለት የጦር መሳሪያ ሌላውን ወገን እያስፈራራ ይገኛል ። ይኸ በጎጥ የተደራጀ ኃይል በገዳይ - አስገዳይነት ሚና የሚንቀሳቀስ ጠበንጃ -ነካሽና አክራሪ ብሄረተኛ ፤ ህግ ጣሽ- ሠላም አደፍራሽ ነው ፡-

እኔ ቤተ መንግሥት ካልገባሁ፤ ኢትዮጵያ መገንጥሏ አይቀርም በሚል ማስፈራሪያ እያሸበረ ያለ ኃይል ነው። አደገኛነቱ ቀላል እንዳልሆነ ሌላውን ሁሉ ለማሳመን የሚጥር፤ የጉራማሌ ስብዕናን ተላብሶ፤ የሀገሪቱን ፖለቲካ እየበወዘ ይገኛል። ይኸ አዋኪ ታጣቂ ቡድን፤ በህግና

ደንብ አማካኝነት የሚቆጣጠረው ኃይል ካላጋጠመው በስተቀር ፤ ሕዝብና ሀገር ሠላም ያገኛሉ ማለት ዘበት ነው ።

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ይህንን ጎራ እያሽሞነሞነውና እያባበለው ስለሆነ፤ የልብ ልብ ተሰምቶታል። " **ባለጌን ሲያከብሩት የፈሩት ስለሚስለው"** እንደ ሰፈር ዐውራ ዶሮ ራሱን አንቱ ብሎ ያካባቢውን ሠላም ነስቷል ። በህግና ደንብ አቅሙን እንዲያውቅ መደረግ ይኖርበታል። በህግና ድንብ ስር መተዳደር ግዴታው ነው !

**3ኛ.** ላለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት፤ ለኢትዮጵያ ጥፋትና ውርደት ፤ ለልጆቿ ዕልቂት፤ ለሀብቷ ውድመት፤ ለዜጎቿ ስደትና መከራ ተጠያቂ የሆነው ወያኔና ተባባሪዎቹ ናቸው። ይኸ ቡድን አከርካሪው የተሰበረ መስሎ ቢታይም፤ ናላው ገና አልተጨረመተም ። በሕዝብ ትግል ከሥልጣን የተገፈተረ እንደሆነ ሊያምን አልተዘጋጀም ። ወደ መቀሌ ሸሽቶ በመመሸግ ፤ በአልሞት- ባይ ተጋዳይነት እየተፍጨረጨረ ይታያል። የተነጠቀውን ሥልጣንና ሃብት እንደገና ለማግኘት ተስፋ በሌለው ተስፋ ውስጥ ያልማል ። ራሱ የመሰረተውን የፌደራል መዋቅር እንኳ ሊያከበር ተስኖታል። ወያኔ የትግራይን የበላይነት ኅልም እስካላረጋገጠ ድረስ ፤ የአፍራሽነት ሚናውን ይቀጥላል።

በማዕከላዊውና በክልሉ መካከል ያለውን የሥልጣን ሰንሰለትና ጠገግ ሊያከብር አለመቻሉን በድርጊት እያስመሰከረ ይገኛል። አዲስ አበባ ያለው በድን ፓርላማ ያሳለፈውን ውሳኔ፤ የወያኔ ክልል አፈንጋጮች አሻፈረን ብለው አላከበሩትም። ይልቁንም፤ ለሌላ ጦርነት እንደሚዘጋጁ አስፈራርተዋል። ይኸንን ለማለት የልብ ልብ የተሰማቸውም፤ በሱዳንና በሌሎች ባለሥልጣኖች ተባባሪነት የጦር መሳሪያ በገፍ ስለሚያገኙ ነው ። የህገራችንንም መሳሪያና ጠቅላላ ንብረት ወደ ትግራይ አጋግዘዋል።

**4ኛው.** ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ። ፍልሚያው፤ ከላይ ከአንድ እስከ ሦስት ተራ ቁጥሮች በተዘረዘሩትና በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የሚካሄደው ነው ። የትግሉ ሂደትና ግብ፤ ባንድ በኩል፤ ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አስተዳደር ዕውን እንዲሆን መታገል ሲሆን፤ በሌላ በኩል፤ በነፍጥ ኃይል፤ ሀገር ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሕዝብን አብሮ መኖር የማሳጣት ሂደት ሆኗል ።

ከእንግዲህ ወዲህ፤ መላው ሕዝባችን በሀገር ውስጥ ጦርነትን ማየት ቀርቶ ፤ መስማትን እንኳ አይፈልግም ። ላለፉት አምሣ ዐመታት ፤ በተለያዩ ተፋላሚዎች ምክንያት የንጽሃን ዜጎች ደም በግፍ ፈስሷል። ዕልፍ አዕላፍ ኢትዮጵያውያን አልቀዋል። ግምቱ በውል የማይገመት የሀገር ኀብት ንብረት ወድሟል ።ብዙ የተማረ ዜጋ ህይወት ተቀጥፏል ። መተኪያ የማይገኝላቸው አያሌ ምሁራን ፤ ዐዋቂዎችና፤ ብርቅየ ጀግና ሰማዕታት፤የከንቱ ከንቱ ሆነው አልፈዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተሰድደዋል። ሕዝብ ግን ሙብቱንና ሀገሩን ለማስከበር ሁለገብ ትግል ማካሄዱ አሁንም የግድ ሆኖበት ይገኛል ።

በዚኽም ሆነ በዚያ ፤ ሀገራችን በብዙ ረገድ ተጎድታለች ። የዚህ ምክንያቱ በአመዛኙ፤ የነፍጥ ፖለቲካ የበላይነቱን በማስፈኑ ምክንያት ነበር። የምክንያቱ መሠረታዊው ምንጭ ግን፤ የአምባገነኖች አገዛዝ ነበር ። በዴሞክራሲ ዕጦት ምክንያት፤ሁሉም የየራሱን የትግል ዘዴና ስልት እየመረጠ በመጓዙ ፤ሌላው ቀርቶ ሊያስማማ በሚያስችለው በጋራ ዐላማ ላይ እንኳን መስማማት አቅቶት የማይተካ ጊዜና ዐቅም በከንቶ ባክኖ ቀረ። አሁንም ቢሆን፤ ገና ካለፈው ስህተት መማር አልቻለም። በተለይ ደግሞ፤ ዐላማችንን በጦር መሳሪያ እናሳካለን የሚሉ ብሄርተኞች በጦር መሣሪያ ኃይል እየተጠቀሙ፤ የብዙሃን ንፁህ ደም በግፍ እንዲፈስ ምክንያት ሆነዋል ። ይኽ ሁኔታ በውድም ሆነ በግድ መቆም አለበት። ከእንግዲህ ወዲያ የሀገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፈታት ያለባቸው፡-

***ሀ.*** በሠላምና በመግባባት፤ በዕውቀትና በሕዝባዊ ፖለቲካ አግባብ እንጅ ፤ በጠብ፤ በዕልኽና ፤ እኔ ላሸንፍ፤ አንተ ተሸነፍ በሚል አምባገነነት ሊሆን አይችልም። ሰጥቶ መቀበልን እንጅ፤ ነጥቆ መጠቀምን ታሳቢ ያድረገ ፖለቲካ ፤ሠላምንና መረጋጋትን አያስገኝም። ሌላ ጦርነትና ጥፋትን ከማምጣት በስተቀር !

**ለ.** በአምክንዮ(ሎጂክ ) ላይ የተመሰረተና ምክንያታዊ ውይይትን የሚያስተናግድ የጋራ ስብሰባ፤ አትራፊ ውጤትን ያስመዘግባል። እስካሁን ሲደረግ የኖረው፤ አካሳሪ እንጅ አተራፊ እንዳልነበረ መረዳት፤ ለወደፊቱ መልካም ውጤት አስመዝጋቢ ውይይት በር -ከፋች ይሆናል ። " ያንዱ ጥፋት ለሌላው ህይወት" የሚመስላቸው ክፍሎች ፤ ኢትዮጵያን በማጥፋት፤ ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ ይሞክራሉ። ጥረታቸው ግን አይሳካም። በረዥሙ ታሪኳ፤ የሀገራችን ጠላቶች መጥፋታችንን እንጅ፤ ኀልውናችንን ፈልገውት አያውቁም። ይኽ ወደ ሀገራችን እየጎረፈ የሚገባው የጦር መሳሪያ ጋጋታ፤ ለጥፋታችን ከሚደገሰልን ልዩ ልዩ ተንኮሎች መካከል አንዱ ክፍል መሆኑንን ተገንዝበን የጋራ መከላከያ ዘዴ

መፈለግ አንገብጋቢ እንደሆነ ልንረዳው ይገባናል ። ከቁጥጥር ውጭ እየሆነ የሚገባው የጦር መሳሪያ የተለያየ ዓላማና ግብ ያላቸው ኃይሎች ዕቅዳቸውን ለማስፈፀም ወደኋላ ስለማይሉ፤ እናም ደግሞ፤ ማንም ሊገታቸው የሚችል ተከላካይ ኃይል አለመኖሩን ሲገነዘቡ፤ አመቺውን ጊዜ በመጠቀም ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በዕርሱ እንዲተላለቅ እሳቱን እያቀጣጠሉት እንደሆነ ማወቅ ይገባናል ።

የጦር መሳሪያ ያለ ህግና ደንብ ቁጥጥር በብዛት የሚገባ ከሆነ ፤ ሀገራችን የመንጠር እሳት ሆና ትቀራለች ብሎ መስጋት የሁሉም ሠላም ወዳድ ዜጋ ጭንቀት ሊሆን ይገባል። በተለይም ደግሞ ፤ እነኝኽ ታጣቂዎች፤ የሕዝቡን የለውጥ እንቅስቃሴ ሂደት በማደናቀፍ በኩልም ያልተጠበቀና ድንገተኛ አደጋ ማምጣታቸውን ይቀጥሉበታል ። ይኽ እንዲሳካ ደግሞ፤ አድፍጠው የተንኮል ተግባር የሚጎነጉንት የወያኔ መሪዎች ተግተው እንደሚሰሩ ፤ አፈትልከው የሚወጡት መረጃዎች ሁሉ ያስጠንቅቃሉ ።

በዘመናት ፤ በቋንቋም ሆነ በኃይማኖት ፤ በባኅልም ሆነ በታሪክ ፤ በጋብቻም ሆነ በተለያዩ መስተጋብሮች አብሮ የኖረውን የጎንደር ክፍለ ሀገር ዜጋ ፤ ቅማንትና ዐማራ ብሎ በመከፋፈል ለጥቂት ጋሻ-ጃግሬዎቹ ጦር መሳሪያ አስታጥቆ፤ የሠላማዊ ዜጎችን ህይወት እንዲጠፋ የሚያደርግ ወያኔ ነው ። የአካባቢው ነዋሪዎች ይኽንን ተገንዝበው አደጋውን መከላከል ይጠበቅባቸዋል ። **ውሃ -ውሃው ሃጅ፤ አለቱ ቀሪ** መሆኑን ተገንዝበው፤ ከወያኔ ወጥመድ ውስጥ የገቡ ሁሉ ሊያስቡበት ይገባል ። የጦር መሳሪያ ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ወደ ሀገራችን በብዛት መምጣት አንደኛው ምክንያት ፤ በሚከሰተው ሕዝባዊ ብጥብጥ ፤ በሕዝብ ትግል ድል ምክንያት ጥቅማቸውንና ሥልጣናቸውን የተነጠቁት ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድኖች፤ እንደገና ለመንሰራራት የሚያደርጉት የሞት -ሽረት መፍጨርጨር ነው። ለጊዜው ችግር የሚፈጥሩ መሆናቸው ባይዘነጋም፤ በመጨረሻ የሚያሸንፈው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ብቻ እንደሆነ አምኖ መቀበል፤ ከታሪክ ወቀሳ ያድናል።

ከላይ የተዘረዘሩት ድምር ውጤት፤ ሀገሪቱን የሚገዟት ቡድኖች፤ የቱን ያኅል፤ ሥልጣን፤ ኃይልና ቁጥጥር እንደሌላቸው አመልካች ሆኗል ። የራሳቸውን ህግና ደንብ እንኳን ለማስከበር ያለመቻላቸውን በግልጽ የሚያመለክት ከመሆኑ አልፎ ተርፎ፤ ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄዱም እንኳን በአንክሮ ለማስተዋል ተስኗቸዋል። ያማ ባይሆን ኖሮ ፤የሀገራችን ሁኔታ ሌላ መልክ በያዘ ነበር። ።

የኢትዮጵያን የለውጥ አካሄድ ፤ አሁን ካለበት አደገኛ አዝማሚያ ለማዳን እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል። ስርኣተ-አልበኝነት ፤ ሀገር አጥፊ እንጅ አልሚ አይደለም። ብልጎ ዜጋ ፤ ከሶርያ፤ ከየመን፤ ከሶማሊያ ፤ከአፋጋኒስታንና፤ ከሊቢያ ሁኔታ ሊማር ይገባዋል። ጠባብ ብሄርተኝነትን በአገዛዙ ደረጃ ማናፈስና ማስፋፋት መቆም አለበት ። ለአንድ ሀገርና ሕዝብ ፤ መሠረታዊ ሕይወቱ ዋስትና ሊያገኝ የሚችለው፤ ዴሞክራሲዊ ሥርዓተ መንግሥት ሲቋቋም ብቻ ነው። ያን ዕውን ለማድረግ፤ የሕዝብ እንቅስቃሴና ትግል ወሳኝ ነው። ወደ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የሚወስደው የሽግግር ሂደት እውን እንዲሆን ሁሉም የሚፈልገውና የሚመኘው ነው ። በአሁኑ ወቅት የታጠቁ ኃይሎች በየቦታው የሚፈጥሩት ግጭቶች ለሽግግር ሂደት እንቅፋት መሆናቸው ግልጽ ነው። ስለሆነም ይህን የሕዝብ የርስ በርስ ግጭት ማስቆም የሁላችንም ግዴታ ሊሆን ይገባዋል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !
ጸረ ሕዝቦች ይቸነፋሉ !!